# የአዲስ አበባ ከተማ ተማሪዎች የዲሲፒሊን መመሪያ ቁጥር 150/2016

Addis Ababa City Students Discipline Directive No. 150/2016

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
Addis Ababa City Administration Education Bureau

የካቲት 18፡ 2016

ተማሪዎች በትምህርት ቤት በጥሩ ሥነ-ምግባር በመታነጽ ለራሳቸው ለማህበረሰባቸው እና ለሀገራቸው ጠቃሚ ዜጋ ሆነው ሊቀረጹ የሚገባ በመሆኑና አሁን እየታየ ያለው የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ችግር በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ የመጣ በመሆኑና ይህንን ችግር ከወዲሁ ማስተካከልአስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ተማሪዎች መልካም ምግባርን በመላበስ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ተቆርቋሪ ችግር ፈችና መልካም ስነ ምግባር ያላቸው ዜጐች ሆነው እንዲቀረጹ ለማስቻልየትምህርት ቤታቸውን ህግና ደንብ በማክበር በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የመማር ማስማር ሂደቱ ሳይታወክ እና የትምህርት ቤቱ ሠላምና ደህንነት ተጠብቆ እውቀት የሚቀስሙበት ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ የተማሪዎች የዲሲፒሊን መመሪያ ቁጥር 150/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ከተማ አስተዳር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
2. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
3. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፤
4. **"የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት"** ማለት ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ባለው የትምህርት እርከን ውስጥየማስተማር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤
5. **"የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት"** ማለት ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ባለው የትምህርት እርከን ውስጥ የማስተማር አገልግሎት የሚሰጥ ነው፤
6. **"ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት"** ማለት ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ባለው የትምህርት እርከን የማስተማርአገልግሎት የሚሰጥ ነው፤

7. "**አዳሪ ትምህርት ቤት**" ማለት ለከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ በቀጥታ ተጠሪ የሆኑትን የልጃገረዶች እና የወንዶች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነው፤

8. ‹‹**የሳይንስ ሼርድ**›› ማለት እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሣይንስ ትምህርት የሚማሩበት ትምህርት ቤት ማለት ነው

9. "**ተማሪ**" ማለት በአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ ባለቤትነታቸው በማንኛውም  አካል የሆኑ የአንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመደበኛ፤በማታ እና በርቀት የትምህርት ፕሮግራም የሚማሩ ማለት ነው፡፡

10. "**ትምህርት ቤት**" ማለት ማንኛውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ የመንግስት እንዲሁም በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ቁጥጥር የሚደረግባቸው መንግስታዊ ያልሆነ ፤የግል ፤የሚሽን፤የቤተ ክርስትያን ፤የመስጊድ እና የህዝብ ት/ቤት ማለት ነው፡፡

11. "**የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ**" ማለት የመማር ማስተማሩ ስራ የሚከናወንበት ስፍራ ማለት ነው፡

12. "**የተማሪ ዲስፕሊን ኮሚቴ**" ማለት ተማሪዎች የዲሲፕሊን ግድፈት ፈጽመው በሚገኙበት ጊዜ ህግና መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ውሳኔ ለመስጠት በት/ቤት ደረጃ የሚቋቋም ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

13. "**የተማሪዎች የደንብ ልብስ**"ማለት በመንግስት ት/ቤቶች በከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ የተመረጠ ለተማሪዎች መለያነት የሚያገለግል ተመሳሳይየጨርቅ ቅርፅ፤መጠን፤ጥራት እና አዘገጃጀት ያለው ልብስ ሲሆን በመንግስታዊ ያልሆነ ፤የግል፤የሚሽን፤የቤተክርስትያን፤የመስጊድ እና የህዝብ ት/ቤት ደግሞ በጋራ ስምምነት የተመረጠ ሆኖ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ የደንብ ልብስ ማለት ነው ፡፡

14. "**ልዩ ፍላጎት**" ማለት በስሜታዊ፣ በባህሪ፣ ወይም በማስተዋል እክል ምክንያት ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ወይም የአእምሮ፣ የመስማት፣ የማየት፣ የመናገር ወይም የመማር እክል ያለባቸው እና እንዲሁም የላቀ የትምህርት ችሎታ ያላቸው ልጆችን እና የአጥንት ወይም የነርቭ እክል ያለባቸው ልጆች የሚያጠቃልሉ ናቸው።

15. "**ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ**" ማለት በተማሪዎች ጉዳይ ላይ በዲሲፕሊን ኮሚቴ የተወሰነ ውሳኔን ይግባኝ ለማየት በትምህርት ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

16. "**የትምህርት ማህበረብ**" ተማሪ፤ ወላጅ፤ ር/መምህራን ፤ሱፐርቫዘር እና ትምህርት ቤቶችን በተለያየ መንገድ ሊደግፉ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍል ማለት ነው፡፡

17. "ጾታዊ ትንኮሳ" ማለት በትምህርት ቤት የሚፈፀም ሆኖ ከሌላው ወገን ፍቃድ ውጪ የሚቀርብ የወሲብ ሀሳብ ወይም ጥያቄ ወይም ሌላ ወሲባዊ ተፈጥሮ ያለው የቃል ወይም የአካል ንኪኪ ተግባር ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) ከሌላው ወገን ፍቃድ ውጪ የመሳም፤ የሰውነት አካን መዳሰስ፤የመጎንተል ወይም የመሳሰለውን የሰውነት ንኪኪ የመፈፀም ድርጊት

ለ) ወሲብ አዘል በሆነ ሁኔታ ተጠቂውን መከታተል ወይም እንቅስቀሴውን መገደብ፤

ሐ) ለውጤት በመቀነስ ወይም ወላጅ እናስመጣለን በማለት በማስፈራራት ወሲብን እንደ ቅደመ ሁኔታ ማስቀመጥ፡፡

3. **የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

4. **የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ትምህርት ቢሮ ሥር በሚገኙ ማንኛውም የአንደኛ፣የመካከለኛ፣ሁለተኛ ደረጃ፣ አዳሪ እና ሳይንስ ሼርድ ካምፓስ ትምህርት ቤቶች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለተማሪዎች መብት እና ግዴታ

5. **የተማሪዎች መብት**

የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል፡-

1. የመማር፣ ጠይቆ የመረዳትና የማወቅ፤
2. ተማሪዎች ከማንኛውም ዓይነት የአካልና ሥነልቦና ጥቃቶች የመጠበቅ፤
3. በትምህርት ቤቱ የትምህርት ግብዓቶች የመጠቀም ወይም አገልግሎት የማግኘት፤
4. የትምህርት ውጤትና የምስክር ወረቀት በወቅቱ የማግኘት፤
5. ስርአትና ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል እና ትምህርት ቤት የመማር፤
6. ሃሳባቸውን የመግለጽና የመደመጥ መብት፤
7. የግል ምስጢራዊ ጉዳዮች የመጠበቅ፤
8. ፆታን መሰረት ካደረገ ጥቃት የመጠበቅ፤
9. የትምህርት ቤቱን ደንብና መመሪያ የማወቅና የማግኘት፤
10. ከመምህራን ድጋፍና እርዳታ የማግኘት፤
11. የሚደርስባቸውን በደልና ቅሬታ በየደረጃው ላሉ የትምህርት ቤቱ አካላት የማቅረብ፤
12. ስለመምህራን የማስተማር ክህሎት በሚዛናዊነት የመገምገም፤ አስተያየት ሲጠየቁ የመስጠት፤
13. ከመማሪያ ክፍል ውጭ የሚከናወኑ የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይየመሳተፍ፤

14.ለተማሪዎች ከሚሰጠው ልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች የመምረጥና የመመረጥ፤

15.ከት/ቤት ወይም በቅርብ ከሚገኝ የጤና ማዕከል የመጀመሪያ የጤና ዕርዳታ የማገኘት፣

16.ልዩ ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ አገልግሎት የማግኘት እና ከጥቃት የመጠበቅ መብት፣

17.በት/ቤት የዕቅድ ዝግጅትና የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ በተወካዮቻቸው አማካኝነት የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡

## 6. የተማሪዎች ግዴታ

በትምህርት ቤትጊቢ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ተማሪ የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1. በት/ቤት በሚወጣው የትምህርት ፕሮግራም መሠረት በመማሪያ ክፍል የመገኘት
2. በሰንደቅ ዓላማ ሥነስርአት ላይ የመገኘትና የመዘመር፤
3. ያለበቂ ምክንያት ከት/ቤት አለመቅረት፣
4. በክበባት የመሳተፍ
5. በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በግልም ሆነ በቡድን በጥሞና የመከታተል፣
6. የክፍል ሥራ የቤት ሥራ የቡድን ሥራ የሚሰጡ የችሎታ መመዘኛዎችን ሠርቶ አጠናቆ በጊዜው የማቅረብ፣
7. የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎችና መምህራን በአግባቡ የሚሰጡትን ድጋፍ ምክርና መመሪያ የመፈፀም፣
8. ሴት ወይም ወንድ ተማሪዎችን ከመተንኮስ፣ ከማስፈራራት ከመድፈር ከመደባደብና ሰብአዊ መብታቸውን ከመጋፋት የመቆጠብ፣
9. ከማንኛውም የቡድን ጸብ አምባጓሮና ጉልበተኝነት ተግባር ራስን ማቀብ፣
10. ለመምህራን፣ ለሠራተኞች፣ ለትምህርት አመራሮችና ለጓደኞቻቸው ተገቢውን ክብር የመስጠት፣ /አለመዝለፍ፣ አለማንጓጠጥ፣ አለመስደብ፣ አለመዛት፣ አለማንቋሸሽ እና የመሳሳሉት/
11. የመማሪያ መጽሐፍትን ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎችን በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም አለማበላሸት፣
12. የትምህርት ቤቱን ንብረት የመጠበቅ /መቀመጫ ወንበሮችን፣ የመማሪያ ክፍሎችን፣ መስኮቶችን፣ ምድረ ግቢውን በንፅህና የመያዝና የመንከባከብ/
13. ማንኛውንም በአካልና በጤና ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሣሪያ ይዞ አለመገኘት፣
14. ማንኛውንም አይነት የሀይማኖትና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች አለማካሄድ፣
15. በትምህርት ቤቱ ያልተፈቀዱ ስብሰባዎች ላይ ያለመሳተፍ፣
16. የግልና የጋራ ንፅህናን የመጠበቅ፤
17. በዚህ መመሪያ በተተደነገገው መሰረት የደንብ ልብስ አለባበስና የፀጉር አያያዝ መጠቀም፤

18. የትምህርት ቤቱን ዩኒፎርም/የደንብ ልብስ አዘውትሮ መልበስ፣
19. አካል ጉዳት ያለበት ተማሪን ጉዳቱን መሰረት ያደረገ አድልዎ አለመፈጸም፤
20. መንግስት ከሚያወጣው እና ህጋዊ በዓላት ውጭ አለማክበር/ዋተር ዴይ፤ክሬዚ ዴይ የመሳሳሉት/
21. በትምህርት ሰዓት ያለ በቂ ምክንያት በት/ቤት ቅጥር ግቢ አለመዟዟር፣
22. የትምህርት ቤቱን አጥር ዘሎ አለመውጣት ወይም አለመግባት ወይም ዕቃ በአጥር አለመቀበልና አለማቀበል፤
23. ሲጋራ አለማጨስ መጠጥ ጠጥቶ አለመገኘት ጫትና ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን አለመጠቀም፤
24. የት/ቤቱን ማህበረሰብና እራሱን ከኤች አይ ቪ ኤድስ የመከላከል፤
25. የስርቆት ወንጀል አለመፈፀም፣ ፈተና መኮረጅ ቁማር መጫወት ከመሳሰሉ ሕገወጥ ድርጊቶችና ከሌሎች ጥፋቶች መራቅ፣
26. መታወቂያ ይዞ የመገኘት ሲጠየቅ የማሳየት፡፡

## 7. የተማሪዎች ዩኒፎርም ወይም የደንብ ልብስ አጠቃቀም

1. የመንግስት ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ዩኒፎርም ወይም የደንብ ልብስ የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ በሚወስነው የጨርቅ ዓይነት፤ጥራት እና ቀለም እና ስፌት ዲዛይን መሆን ይኖርበታል፣
2. መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ዩኒፎርም ወይም የደንብ ልብስ የጨርቅ ዓይነት፤ጥራት እና ቀለም በትምህርት ቤቱ አስተዳደር፤ተማሪዎችና ወላጆች የጋራ ስምምነት ይሆናል፤
3. የወንድ ተማሪዎች የደንብ ልብስ የሱሪ ቩል ስፋት ኖርማልወይም ከ 18 ኢንችያላነሰመሆን አለበት፤
4. የሴት ተማሪዎች የደንብ ልብስ አዘገጃጀት የቀሚስ መጠን ከጉልበት በታች ያለውን 2/3ኛ የእግር ክፍል የሚሸፍን መሆን መሆን አለበት፤
5. ማንኛውም ተማሪ ከተወሰነው የደንብ ልብስ ዓይነት፤ጥራትና ቀለም ውጪ መጠቀም የለበትም፣
6. ከትምህርት ቤቱ ህጋዊ ፈቃድ ውጪ ማንኛውንም ዓይነት ፅሁፍ ማሳተም፤ሌላ የጨርቅ ዓይነት ቀጥሎ ማሰፋት እና ያልተፈቀደ የደንብ ልብስ ዓይነት ፤ቅርፅና ይዘት መጠቀም የተከለከለ ነው፤
7. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 6 የተዘረዘሩት ግዴታዎች የማታ እና የርቀት ተማሪዎችን አይመለከትም፡፡

## 8. የፀጉር አቆራረጥ፣ አያያዝ እና የጆሮ ጌጥ

ማናኛውም ተማሪ ከዚህ በታች

1. ማንኛውም ተማሪ የፀጉርን ንፅህና መጠበቅ አለበት፣
2. ማንኛውንም አይነት የፀጉር ቀለም መቀባት የለበትም፤
3. ማናኛውም ወንድ ተማሪ ፀጉሩን ከ3 ቁጥር የበለጠ ወይም ከ1 ሴ.ሜትር የበለጠ ማሳደግ የለበትም፤
4. ማናኛዋም ሴት ተማሪ ፀጉሯን ከማበጠርና ከማስያዝ ወይም ሹሩባ ከመሰራት ውጪ ሌሎች ማናቸውም አይነት የፀጉር አሰራሮችን መሰራት የለባትም፤
5. ማናኛውም ወንድ ተማሪ የአንገት፤ የእጅ ሀብል ቀለበት ጉትቻ ማድረግ እንዲሁም ጥፍር ማሳደግ የለበትም፤
6. ማናኛዋም ሴት ተማሪ የአንገት ሀብል፣ የእጅ ጌጥ፣ የእግር ጌጥ፣ ከጋብቻና ከቃልኪዳን ውጪ የሆነ ቀለበት፣ እንዲሁም ከጆሮ ውጭ የትኛውም የሰውነት አካል ላይ ለማጌጥ ተብሎ ማስበሳትና ጌጦችን ማድረግ የለባትም፤

## ክፍል ሦስት

## ዲሲፐሊን እርምጃዎች እና ውሳኔ አሰጣጥ

### 9. የዲሲፐሊን ቅጣት መሰረታዊ ዓላማ

የዲሲፐሊን ቅጣት ዓላማ የትምህርት ቤቱን የመማር ማስተማር ሥራ ውጤታማ ለማድረግ ሲሆን ተማሪው በፈጸመው ጥፋት ወይም የዲሲፐሊን ጉድለት ተጸጽቶ ወደፊት ብቁ እና ታማኝ ዜጋ ለመሆን እንዲችል ለመርዳት፣ ለማረምና ለማስተማር እንዲሁም የማይታረም በሚሆንበት ጊዜ መማር ማስተማሩ እንዳይተጓጎል ከትምህርት ቤት ለማሰናበት ነው፡፡

### 10. ስለ ዲሲፐሊን ቅጣት

የዲሲፐሊን ጥፋት ወይም ጉድለት በፈጸመ ማንኛውም ተማሪ ላይ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፡-

1. የቃል ማስጠንቀቂያ፤
2. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፤
3. ለአንድ ዓመት ከትምህርት ቤት ማገድ፤
4. ከትምህርት ቤት ማሰናበት፡፡

### 11. የቅጣት አይነቶች አመዳደብ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ10 ንዑስ አንቀፅ(1) እና (2) የተደነገጉት ቀላል የዲሲፐሊን ጥፋት ቅጣቶች ሲሆኑ በንዑስ አንቀፅ (3) እና (4) የተደነገጉት ደግሞ ከባድ የዲሲፐሊን ጥፋት ቅጣቶች ተብለው የሚመደቡ ናቸው፡፡

12. **ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች**

1. ትምህርት ቤቱ በሚያወጣው የትምህርት ፕሮግራም መሠረት በወር ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ እንዲሁም በሴምስተር ውስጥ ከ5 ቀን በላይ በሰአቱ ያለመገኘት ያለበቂ ምክንያት ማርፈድ እና መቅረት
2. የመደበኛ የቀን ትምህርት ተማሪ ሆኖ በሰንደቅ ዓላማ ሥነ-ስርአት ላይ አለመገኘት ወይም አለመዘመር፤
3. በተማሪዎች መካከል አላስፈላጊ ጭቅጭቅና ንትርኮች መፍጠር፤
4. የክፍል ውስጥ ሥነ-ስርዓትን ያለማክበር፤መረበሽ፣ መጮህ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማወክ ሆነ ብሎ መብራት ማጥፋት ወይም እንዲጠፋ ተፈልጎ ማብራት፤
5. መምህራንን ወይም የትምህርት ማህበረሰቡን አለማክበር ፤
6. የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎችና መምህራን በአግባቡ የሚሰጡትን ድጋፍ፣ምክር፣ አስተያየት ወይም ትዕዛዝ አለመቀበል ወይም አለመፈፀም፤
7. በፈተና ወቀት ይዘው እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው ተማሪዎች በስተቀር ማንኛውንም የተከለከሉ ቴክኖሎጂዎችን ይዞ ወደ ክፍል መግባት፤
8. በትምህርት ቤቱ ፈቃድ ባልተሰጠው ማንኛውም ስብሰባ መሳተፍ፣
9. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እና በፈተና ወቅት ስልክ፣ታብሌት ይዞ መምጣት፤ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ይዞ መግባት፤
10. በትምህርት ሰዓት ያለ በቂ ምክንያት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ መዟዟር፤
11. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ መታወቂያ ይዞ አለመገኘት ወይም ሲጠየቅ አለማሳየት፡፡

13. **በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ**

1. በትምህርትቤቱ ርዕስ መምህር የሚወከል አንድ ምክትል ርዕሰ መምህር ወይም የክፍል ተጠሪው መምህር የቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፤
2. ርዕሰ መምህሩ የቀላል የዲሲፕሊን ክስ ሲቀርብለትበዲሲፕሊን ኮሚቴ ታይቶ የውሳኔ ሃሳብ እንዲቀርብ ለትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይመራል፤
3. ርዕሰ መምህሩ በኮሚቴው ተመርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ሲቀርብለት ውሳኔ ይሰጣል፤የውሳኔውንም ውጤት ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

14. **ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት**

ለአንድ ዓመት ከትምህርት ቤት የሚያሳግድ ጥፋት፡-

1. በትምህርት ቤት ውስጥ የስርቆት ድርጊት ፈጽሞ መገኘት፣
2. ሴት ወይም ወንድ ተማሪዎችንመተንኮስ፣ ማስፈራራት፣መሳደብና ማንጓጠጥ

3. የትምህርት ቤቱን ጊቢ አጥር ዘሎ መውጣት ወይም መግባት ወይም በጊቢ አጥር በኩል ማንኛውንም ነገር መቀበልና ማቀበል፤
4. ቁማር መጫወት፤
5. ሲጋራ ማጨስ፣ ቬፒንግ/ኢ-ሲጋሬት/፤ ኢ-ሊኩዊድ፣/ መጠቀም የአልኮል መጠጥ ጠጥቶ መገኘት፣ሺሻ ተጠቅሞ መምጣት፣ ጫት ቅሞ መምጣት ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን ተጠቅሞ መምጣት፤
6. ትምህርት ቤቱና ወላጅ ባላወቁት ወይም አሳማኝ ባልሆኑ ምክንያቶች ከትምህርት ቤት በአመቱ የትምህርት ካላንደር 10% መቅረት፤
7. ማንኛውንም የትምህርት ቤቱን ንብረት የሆኑትን የመማሪያ መጽሐፍትን፣ መቀመጫ ወንበሮችን፣ሰሌዳዎችን፤ የፕላዝማ ቴሌቪዥን ፤ሬዲዮን ፤ኮምፒዩተሮች ፤የኢንተርኔት መሰረተ ልማትና ቁሳቁሶችን፤ የመማሪያ ክፍሎችን፣ መስኮቶችን፣ እና ሌሎች የትምህርት ቤት ንብረቶችን በጥንቃቄ አለመያዝ፣ አለመጠቀም ወይም እንዲበላሹ ወይም አገልግሎት እንዳይሰጡ ማድረግ፤
8. በፈተና ወቅት ሁከት መፍጠር ፣ የፈተና ሥርዓቱ እንዲደናቀፍ ማድረግ ፤መኮረጅ ወይም ማስኮረጅ፤
9. የትምህርት ቤቱን መምህራን፣ ሠራተኞችና ኃላፊዎችን መሳደብና ማንጓጠጥ ወይም ለመደብደብ መሞከር፤
10. ተማሪ መደብደብ፣ ንብረት መንጠቅ ወይም ማስፈራራት፤
11. በተደጋጋሚ በቀላል የዲሲፕሊን የተገለፁ ጥፋቶች አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ (2)-(12) በተደጋጋሚ በሴሚስተር ለ2(ሁለት) ጊዜ ተቀጥቶ ባለመታረም የሚፈጸም ቀል የዲሲፕሊን ጥፋትሲኖር፡፡

## 15. ከትምህርት ቤት እስከ መጨረሻው የሚያሰናብት ጥፋት

ማንኛውም ተማሪ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ፈጽሞ ከተገኘ በትምህርት ቤቱ ተማሪ ከመሆን እስከ መጨረሻው ይሰናበታል፡-

1. አደገኛ የሆኑ ስለታማ ወይም የጦር መሳሪያዎችን በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ይዞ መገኘት፤
2. በትምህርት ቤትቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በፈተና ወቅት ስልክ፣ታብሌት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ መጠቀም፤ የፈተና ሂደቱን ሊያውክ የሚችል ተገቢ ያልሆነ ተግባር ማከናወን፤ የተሳሳተ መረጃዎች ማስተላለፍ፤
3. ሴት ወይም ወንድ ተማሪዎችን መደባደብ ወይም ሰብአዊ መብታቸውን መጣስ፤
4. ማንኛውም ወሲባዊ መሳም ወይም ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም፤

5. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ሀይማኖታዊና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ፣
6. በማንኛውም የቡድን ጸብ እና አምባጓሮ ተግባር ላይ መሳተፍ፤
7. ከኢትዮጵያዊ እሴቶች ያፈነገጡ ወይም ህጋዊ ያልሆኑ ሁነቶችን ማካሄድ ወይም በዓላትን ማክበር ወይም መፈጸም፤ ዋተርዴይ፤ ክሬዚ ዴይ፤ እራቁት ቀን ከለር ዴይ፤
8. የትምህርት ቤቱን ንብረት ሆን ብሎ ጉዳት ማድረስ ወይም ለጉዳት ማጋለጥ፤
9. በትምህርት ቤት ውስጥ ሴት ተማሪ መድፈር ወይም በማናቸውም ሁኔታ የትምህርት ቤቱን ሴት ተማሪ ለመድፈሩ በፍርድ ቤት የተወሰነበት ከሆነ፤
10. በፈተና ወቅት ለሌላ ተማሪ መፈተን ወይም ለራስ ማስፈተን፤
11. የተጭበረበረ የትምህርት ማስረጃ አቅርቦ መገኘት፤
12. መምህራንን ወይም የትምህርት ቤቱን ሌሎች ሠራተኞች መደብደብ፤
13. ከዚህ ቀደም ባጠፋው ጥፋት በከባድ ዲስፕሊን ምክንያት ለአንድ ዓመት ከትምህርት እንዲታገድ ቢደረግም በድጋሚ የከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያሰጥ ድርጊት መፈጸም፡፡

## 16. ተማሪ ለግዜው ከትምህርት ታግዶ የሚቆይበት ምክንያት

ማንኛውም ተማሪ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት አጥፍቶ ሲገኝ በሚከተሉት ምክንያች ለግዜው ሊታገድ ይችላል፡-

1. የመማር ማስተማር ሒደቱን የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ
2. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በተማሪዎችና በትምህርት ማህበረሰቡን የሚያውኩ የደህንነት ስጋት እንዳይፈጠር ለመከላከል
3. በጥፋቱ ላይ የተሳተፉ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎችን ክብራቸውን ለመጠበቅ፡፡

## 17. ከትምህርት ገበታ ሊያሳግድ የሚችል የቅጣት አወሳሰን

1. ከትምህርት ገበታ ሊያሳግድ የሚችል ጥፋት በተማሪ መፈጸሙ ሲረጋጥ የክፍል ኃላፊ መምህሩ በየጊዜው የተመዘገበ መረጃ ፤ከወላጅ ጋር የተደረገ ውይይት፣ ተማሪው በድጋሚ ጥፋት ላለመፈጸም የፈረመበት፣ ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት አጠቃላይ የተማሪውን ባህሪ ሊገልፅ የሚችል መረጃ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በኩል ለዲሲፕሊን ኮሚቴ መቅረብ አለበት፤
2. ከላይ የተመለከተውን መነሻ በማድረግ የትምህርት ቤቱ የዲስኘሊን ኮሚቴ በተማሪው ላይ አግባብነት ያለው እርምጃ ይወስዳል፣
3. ተማሪው ከትምህርት ገበታው ከታገደበት ጊዜ ጀምሮ በ 5 ቀን ውስጥ ለዲሲፕሊን ኮሚቴው መቅረብ ይኖርበታል፤
4. ተማሪውን ከትምህርት አግዶ ማቆየት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እግዱ የሚፈጸመው በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ይሆናል፤

5. ውሳኔ ሳያገኝ ከ15 ቀናት በላይ የቆየ ተማሪ ያለምንም ተጨማሪ ሥነሥርአት ወደ ትምህርት ገበታው እንዲመለስ ይደረጋል፤
6. ተማሪው ከትምህርት ገበታው የታገደበትን ምክንያትና ታግዶ የሚቆይበትን ጊዜ እግዱን በሰጠው አካል በጽሁፍ ይገለጽለታል፤
7. እግዱ የማገጃው ትእዛዝ በጽሁፍ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤፡፡

## ክፍልአራት

## ስለዲሲፕሊን ኮሚቴ መቋቋምና አሰራር

### 18. የዲሲፕሊን ኮሚቴ ስለ ማቋቋም

በየትምህርት ቤቱጉዳዮችን እየመረመረየውሳኔ ሃሳብ ለትምህርት ቤቱ ርዕስ መምህር ወይም ምክትል ርዕስመምህር የሚያቀርብ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

### 19. የኮሚቴው አባላት ስብጥር

1. የተማሪየዲሲፕሊን ኮሚቴ ሰባት አባላት ይኖሩታል፤ የኮሚቴው አወቃቀርም እንደሚከተለው ይሆናል፡-
   ሀ) በርዕሰ መምህሩ የሚሰየም አንድ ሰው.......................................ሰብሳቢ፤
   ለ) በርዕሰ መምህሩ የሚሰየም አንድ ሰው.........................................አባል፤
   ሐ) ከተማሪዎች ፓርላማ/ካውንስል 2 ተወካይ አንዷ ሴት.....................አባል፤
   መ) ከትምህርት ቤቱ መሰረታዊ መምህራን ማህበር አንድ ተወካይ.........አባል፤
   ሠ) የወላጅ፣ የተማሪ፣ መምህር ህብረት ተወካይ................................አባል፤
   ረ) የትምህርት ቤቱ የሰው ኃይል አስተዳደር ተወካይ..............አባልና ጸሀፊ፡፡

### 20. የኮሚቴ አባላት መመዘኛ

ማናቸውም የኮሚቴ አባል፡-

1. በጠባዩና በስራ አፈጻጸሙ የተመሰገነ፣
2. ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ በዲሲፕሊን ክስ ቀርቦበት ያልተቀጣ፣
3. መምህራንናሠራተኞች በትምህርት ቤቱ ወይም በተቋሙ ግቢ ውስጥ ቢቻል ከሁለት አመት በላይ አገልግሎት ያላቸው ሊሆን ይገባል፡፡

### 21. የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን

1. ከትምህርት ቤቱ የተመረጡት የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ሁለትአመትይሆናል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሲሆን ተወካዮች ለአንድ ጊዜ በድጋሚ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

### 22. ከኮሚቴው አባልነት ስለመነሳት

1. የኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ማንኛውም አባል ክስ ከቀረበበት ተማሪ ጋር ፀብ ያለው ወይም በስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ከሆነ ወይም ከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ ለዚያ ጉዳይ ብቻ ከኮሚቴው አባልነት እንዲነሳ ይደረጋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) በተገለፀው መሰረት የኮሚቴ ሰብሳቢው ከሰብሳቢነት የሚነሳ ከሆነየቀሩት የኮሚቴ አባላት ከመሃከላቸው ለዚህ ጉዳይ ብቻ ሌላ ሰብሳቢ ይመርጣሉ፤

## 23. የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባልን ስለመሰረዝ

ማንኛውም የኮሚቴ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነቱ ሊሰረዝ ይችላል፡-

1. በግል ችግር ምክንያት በኮሚቴው ያለውን ተሳትፎ መቀጠል ሳይችል ሲቀር፣
2. ከመስሪያቤት ሲለቅ፤
3. በተለያየ ምክንያ ስራውን በአግባቡ ማከናወን አለመቻሉ ሲረጋገጥ፤
4. ራሱን ከጉዳዩ በማግለልና ሌላውን አባል ለማስጠላት የሞከረ ወይም ሚስጥር ያወጣ ወይም ቃለጉ ባኤዎችን መረጃዎችንና ጽሁፎችን ለተከሳሹ ያሳየ ወይም ያጋለጠ ወይም የሰጠ እንደሆነ፣
5. ከኮሚቴ አባልነት በተሰረዘ አባል ምትክ የተሰረዘው የኮሚቴ አባል በተመረጠበት ወይም በተመደበበት መንገድ አዲስ ሌላ አባል ይተካል፡፡

## 24. የኮሚቴው ምልአተ ጉባኤና ድምጽ አሰጣጥ

1. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ሰብሳቢውን ጨምሮ ከግማሽ አባላት በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤ ከተገኙ አባላት ቢያንስ አንዱ የተማሪ ተወካይ መሆን ይኖርበታል፤
2. ኮሚቴው ሰብሳቢ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቢቀር የቀሩት አባላት ከመካከላቸው ለጊዜው ሰብሳቢ ይመርጣሉ፤
3. ማንኛውም የኮሚቴው ውሳኔ የሚሰጠው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡እኩል ድምጽ ሲሆን ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፤የልዩነት ሀሳብ በቃለ ጉባኤ ይሰፍራል፡፡

## 25. ስለ ዲሲፕሊን ክስ አመሰራረት

1. የዲሲፕሊን ክስ አመሰራረትና ጉዳዩ በዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲታይ በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወይም ምክትል ርዕሰ መምህር ሲወሰን በትምህርት ቤቱ የሰው ኃይል አስተዳደር አማካይነት የዲሲፕሊን ክሱን ይመሰረታል፤
2. የዲሲፕሊን ኮሚቴው ሰብሳቢ የዲሲፕሊን ክስ ተዘጋጅቶ ማስረጃዎቹ ተጠናቀው ሲቀርብለት ተከሳሹ ለቀረበበት ጥፋት መልስ በጽሁፍ እንዲሰጥ መጥሪያ ይልክለታል፤
3. የሚላከው መጥሪያ ክሱ የሚሰማበትን ቀን ሰአትና ቦታ የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ፣የሰነድ ማስረጃ የያዘ መሆን አለበት፤

4. ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ መልስና የመከላከያ ማስረጃ የሚያቀርብበትን ጊዜ የክሱ ጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ለቀላል ዲሲፕሊን በአምስት ቀን ለከባድ 7 ቀን ውስጥ ማቅረብ አለበት
5. ተከሳሹ የዲሲፕሊን ኮሚቴ የላከለትን መጥሪያ ሆን ብሎ ሊቀበል ያልቻለ እንደሆነ በኮሚቴው ስብሰባ ላይ የሚገኝበት ቀን ሰአትና ቦታ ተገልጾ የጥሪ ማስታወቂያ ለአምስት ተከታታይ ቀናት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ እንዲቆይ ይደረጋል፤ በተወሰነ ጊዜ ተከሳሹ ካልቀረበ ተከሳሹ በሌለበት ክሱ ተሰምቶና ተመርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤
6. የዲሲፕሊን ኮሚቴው የዲሲፕሊን ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሃሳብ ለትምህርት ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 26. የዲሲፕሊን ኮሚቴ አሰራር

1. ኮሚቴው በዚህ መመሪያ የተሰጠውን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ የሚያስፈልጉትን ማህደሮች፣ መረጃዎችና ሰነዶች አስቀርቦ ማየት እንዲሁም አግባብነት ያለውን የሰው የምስክር መጥራትና መስማት ይችላል፣
2. ኮሚቴው በተማሪውላይ የቀረበውን ክስ በሚያጣራበት ጊዜ፣

ሀ. የተከሳሹ ሙሉ ስም ከነአያት ያረጋግጣል፣

ለ. ተከሳሹ የተከሰሰበትን ጭብጥ፣

ሐ.ክሱን ያረጋግጣሉ ተብለው የቀረቡትን የጽሁፍ ሆነ የሰው ምስክርነት ማስረጃዎች፣

መ. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚገኘውን የተከሳሹን የግል ማህደር፤ለቀረበው ክስ አግባብነት ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦችና፣ መመሪያዎች፤ የጽሁፍና የሰው ማስረጃዎች፤አግባብነት አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን ማስረጃዎች እንደአስፈላጊነቱ በማስቀረብ ይመረምራል፡፡

## 27. የቀረበውን ክስ ስለመመርመር

1. ለተከራካሪ ወገኖች፣ለምስክሮችና ለሌሎች አስረጂዎች የሚሰጡ መጥሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ደብዳቤዎች የተዘጋጁና ሰብሳቢው እየፈረመባቸው ለሚመለከተው ተማሪ መድረሳቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
2. ለተከሳሹ ክሱና ማስረጃው በጽሁፍ እንዲደርሰውና የመከላከያ መልሶችን በጽሁፍ የማቅረብ መብት የተጠበቀለት መሆኑን ያረጋግጣል፤
3. የከሳሹ ምስክሮች ሲቀርቡ ተከሳሹ በተገኘበት ቃላቸውን እንዲሰጡ ያደርጋል፤ ተከሳሹም የመስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብቱን ያስጠብቃል፤ የተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ በሚሰማበት ጊዜ ከሳሽ ተገኝቶ የመስቀለኛ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፤
4. ተከሳሹ የመደመጥ፣ የመከራከርና በበኩሉ የመከላከያ ማስረጃዎችና ክርክሮቹንም የማቅረብ መብቱ ተጠብቆ ክሱ በማስረጃ እንዲጣራ ያደርጋል፤

5. የዲሲፕሊን ኮሚቴው ከተፈጸመው የዲሲፕሊን ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ ቅጣት ይሰጣል፤
6. የስብሰባው ቃለ ጉባኤ በትክክልእየተጻፈና እየተዘጋጀ አባላቱም እንዲፈርሙበት ሆኖ በጥንቃቄ መቀመጥ አለበት፤
7. ከሳሽና ተከሳሽ እንዲሁም ምስክሮች የሚሰጡትን ቃል በትክክልና በጥንቃቄ መመዝገብና ቃል ሰጭዎች በስብሰባው መጨረሻ ላይ እንዲፈርሙበት ያደርጋል፤
8. በሁለቱም ወገን የሚቀርቡ ማስረጃዎች ተመዝግበውና ለኮሚቴው ቀርበው ከታዩ በኋላ ፋይሉን አደራጅቶ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፤

## 28. በተከሳሽ ስለሚቀርብ የጽሁፍ ማስረጃ

1. ተከሳሹ ለተነገረበት ጥፋት መከላከያ የሚሆነውን የጽሁፍ ማስረጃ ወይም ምስክሮች ማቅረብ ይችላል፤
2. ተከሳሹ እንዲቀርብለት ወይም ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቃቸው የጽሁፍ ማስረጃዎች፣ከጭብጡ ጋር አግባብነት ያላቸውን መሆኑን ሲያምንበት እንዲቀርብ የሚመለከተውን ክፍልሊጠይቅ ይችላል፤
3. ትምህርት ቤቱ በኮሚቴው ሲጠየቅየጽሁፍ ማስረጃ አቅርቦ የማሳየት ወይም ትክክለኛ ግልባጩን የመስጠት ግዴታ አለበት፤
4. ተከሳሹ ጭብጡን የሚያስረዱለት ምስክሮች እንዲጠሩለት ስማቸውንና አድራሻቸውን ዘርዝሮ ጥያቄውን ካቀረበ ኮሚቴው እንዲጠሩና ቀርበው እንዲመሰክሩ ለማድረግ ይቻላል፡፡

## 29. የዲሲፕሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ አቀራረብ

1. ኮሚቴው የቀረበለትን የከባድ የዲሲፕሊን ክስ መርምሮ የውሳኔ ሃሳቡን ለትምህርት ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፤
2. የዲሲፕሊን ኮሚቴው የቀረበለት የዲሲፕሊን ጉዳይ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ውድቅ መሆኑን ከነምክንያቱ በመዘርዘር የውሳኔ ሃሳብ ለትምህርት ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፤
3. የትምህርት ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከዲሲፕሊን ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ በደረሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤ውሳኔው ወዲያውኑ ለተከሳሹ በጽሁፍ መሰጠት አለበት፡፡
4. የዲሲፕሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ በትምህርት ቤቱ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ አርፎበት በጽሁፍ ለተከሳሽ እስኪሰጥ ድረስ በሚስጢር መጠበቅ አለበት፤
5. የዲሲፕሊን ኮሚቴው ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ የትምህርት ቤቱ የበላይ ኃላፊ በ5 (አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለተከሳሹ በጽሁፍ እንዲሰጠው መደረግ አለበት፡፡

30. **የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ**

1. የዲሲፕሊንቅጣትየማንኛውንምፍርድቤትውሳኔሳይጠብቅወይምሳይከተልሊወሰንይችላል፤
2. ተከሳሹ በተደጋጋሚ ከ2 (ሁለት) ጊዜ በላይ በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት የተቀጣ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴው በከባድ ዲሲፕሊን ጥፋት ሊወሰን ይችላል፡፡

31. **የዲሲፕሊን ቅጣት በሪከርድነት ስለሚቆይበት ጊዜ**

1. ለቀላል ዲሲፕሊን ቅጣት ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለአንድ አመት፤
2. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት ይሆናል፡፡

32. **ስለይግባኝ**

1. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የዲሲፕሊን ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢነት በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የጸደቀ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተማሪ ይግባኙን ትምህርት ቤቱ ከሚገኝበት ከወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ጀምሮ፤ ክፍለ ከተማ እስከ ትምህርት ቢሮድረስ የስልጣን እርከኑን ጠብቆ ማቅረብ ይችላል፤የትምህርት ቢሮ ውሰኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡
2. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የዲሲፕሊን ኮሚቴ የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢነት በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የጸደቀ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተማሪ ይግባኙን ትምህርት ቤቱ ለሚገኝበት ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት፤ ፤ትምህርት ቢሮ ድረስ የስልጣን እርከኑን ጠብቆ ማቅረብ ይችላል፤ የትምህርት ቢሮ ውሰኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡
3. የትምህርት ቢሮ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተማሪ ይግባኙን አግባብ ባለው ፍርድ ቤት ለማቅረብ ይችላል፡፡

33. **የይግባኝ አቀራረብና የጊዜ ገደብ**

ሀ) ይግባኝ ባይ የሚያቀርበው የይግባኝ ማመልከቻ ይግባኝ የታባለበት ውሳኔ ላይ ተቃውሞ የቀረበበትን ምክንያትና ይግባኝ ባዩ እንዲሰጥለት የሚፈልገውን ውሳኔ በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡

ለ) ለወረዳ ት/ቢሮ ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው ውሳኔው በደረሰው በ5 (አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

ሐ) በዚህ አንቀፅ 33(ሀ) ወይም(ለ) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ ይግባኝ ባዩ ከአቅም በላይ የሆነበትን ምክንያት ከተወገደበት ቀን ጀምሮ በ5 (አምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኝ እንዲያቀርብ ለይግባኝ ሰሚው አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡

መ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ(ሐ) መሰረት ጊዜው ካለፈ ቦኃላ ይግባኝ እንዲቀርብ ለማስፈቀድ የሚቀርብ ማመልከቻበጊዜው ይግባኝ ለማቅረብ ያልቻለበትን ምክንያት በዝርዝር የሚገልፅ መሆን አለበት፤ ደጋፊ ማስረጃ ካሉ መያያዝ አለባቸው፡፡

ሠ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) መሰረት የቀረበውን ማመልከቻ 5(በአምስት) የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም እና የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት

### 34. ዓላማ

1. ለቅሬታዎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት፣
2. ለቅሬታዎች መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን በማረም፤ እና
3. ሁሉንም በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችልና ፍትሀዊ የሆነ አሰራር በማስፈን የሰመረ ግንኙነት እንዲዳብር ማድረግ ይሆናል፡፡

### 35. ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. በማንኛውም የትምህርት ተቋምቅሬታ ወይም አቤቱታን ተቀብሎ በመመርመር ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ይቋቋማል፤
2. የዲሲፒሊን ኮሚቴ አባል የሆነ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ሆኖ ሊሰየም ወይም ሊወከል አይችልም፡፡

### 36. አባላት

1. የተማሪዎች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሰባት አባላት ይኖሩታል፤ የኮሚቴው አወቃቀርም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) በርዕሰ መምህሩ የሚሰየም አንድ..................................................ሰብሳቢ፤

ለ. ከተማሪዎች ፓርላማ/ካውንስል 2 ተወካይ አንዷ ሴት.........................አባል፤

ሐ. ከትምህርት ቤቱ መሰረታዊ መምህራን ማህበር አንድ ተወካይ...............አባል፤

መ. ከትምርት ቤቱ የሥርዓተ ጾታ ተወካይ አንድ.......................................አባል፤

ሠ) የወላጅ፣ የተማሪ፣ መምህር ህብረት አንድ ተወካይ.............................አባል፤

ረ. የትምህርት ቤቱ የሰው ኃይል አስተዳደር ተወካይ.....................…...አባልና ጸሀፊ፤

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የኮሚቴው አባላት የሚሰየሙት ከትምህርት ቤቱ ይሆናል፡፡

### 37. የቅሬታ ኮሚቴ አባልነት መመዘኛ

ማናቸውም የኮሚቴ አባል፡-

1. በመልካምሥነ ምግባሩና በሥራ አፈጻጸሙ የተመሰገነ፣

2. ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ በዲሲፕሊን ጉድለት ያልተቀጣ፣
3. ከተማሪዎችናወላጅ ተማሪ ህብረት ቋሚ የመንግስት ሠራተኛ የሆነና በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ከሁለት አመት በላይ አገልግሎት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡

## 38. የቅሬታ ኮሚቴ የአገልግሎት ዘመን

1. የኮሚቴ አባለት የአገልግሎት ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፤ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝማንኛውም አባል እንደገናለአንድየአገልግሎት ዘመን ሊመደብ ወይም ሊመረጥ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የቅሬታ ኮሚቴ አባል የአገልግሎት ጊዜው ሳይደርስ በሌላ ሊተካ ይችላል፡፡

## 39. የቅሬታሰሚ ኮሚቴ ስብሰባ

1. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለስራው ባስፈለገ መጠን በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. በኮሚቴው ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤይሆናል፤
3. የኮሚቴው ውሳኔ የሚያልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ ውሳኔ ይሆናል፤ በሀሳብ የተለየው አካል የተለየበትን ምክንያትበቃለ ጉባኤው በግልጽ እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

## 40. ከቅሬታ ኮሚቴ አባልነት ስለመነሳት

ማንኛውም የኮሚቴ አባል ክስ ከቀረበበት ተማሪ ጋር ፀብ ወይም የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም የጥቅም ግጭት ሲኖረው ለዚያ ጉዳይ ብቻ ከስብሰባው መነሳት አለበት፡፡

## 41. ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባልነት ስለመሰረዝ

ማንኛውም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 40 በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከኮሚቴ አባልነት ሊሰረዝና በምትኩ ሌላ አዲስ አባል ሊተካ ይችላል፡፡

## 42. ቅሬታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም በመማር ማስተማሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግኑኝነት ያለቸው (አስተማሪ ፣ተማሪ እና በትምህርት ቤቱ ቅጠር ግቢ ውስት ሆነ ውጭ) ህጋዊ መብቴ ተጓድሎብኛል ወይም በደል ተፈፅሞብኛል በማለት ቅር የተሰኘ እንደሆነ ቅሬታውን እንዲታይለትና የመፍትሂ እርምጃ እንዲወሰድለት ት/ቤቱን መጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤
   ሀ) በህጎችና መመሪያዎች አተረጓገም ወይም አፈጻፀም
   ለ) ከመብቶች እና ጥቅሞች አጠባበቅ

ሐ) ከት/ቤት አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ሁኔታዎች

መ) ከዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ ከሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዬች ጋር በተያያዘ ምክንያት በደል ደረሰብኝ የሚል አካል ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 43. የቅሬታ ማመልከቻ

1. ቅሬታው እንዲታይለት የሚፈልግ ማንኛውም ተማሪ የቅሬታ ማመልከቻውን ለመስሪያ ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለማቅረብ ይችላል፤የቅሬታ ማመልከቻው የሚከተለውን መያዝ አለበት

   ሀ. የአመልካች ስምና አድራሻ፣

   ለ.የክፍል ደረጃ እና ሴክሽን፣

   ሐ.የቅሬታ የቀረበበት አካል፣

   መ.የቅሬታው መንስኤ፣

   ሠ.ደጋፊ ማስረጃዎች፣

   ረ.የሚሻውን መፍትሄ፣

   ሰ.ቀንና ፊርማ መኖር አለበት፤

2. የቅሬታቸው መንስኤ አንድ አይነት የሆነ የቅሬታ ማመልከቻቸውን በተወካያቸው አማካይነት በቡድን ሊያቀርቡ ይችላሉ፤

## 44. ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ

1. ቅር የተሰኘ ተማሪቅር የተሰኘበትን ጉዳይ ከተከሰተበት ወይም ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለትምህርት ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቅሬታውን ማመልከቻ ሊያቀርብ ያልቻለ ተማሪ ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት በተወገደ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 45. ቅሬታውን ስለማጣራት

1. የትምህርት ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማመልከቻ ሲቀርብለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 የተደነገገውን አሟልቶ የቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ ተቀብሎ ይመዘግባል፡፡
2. ኮሚቴው ፡-

   ሀ. የቅሬታ ማመልከቻውንና አግባብ ያላቸውን ማስረጃዎች ይመረምራል፤

   ለ. ከአመልካቹ እና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከሰጠው የስራ ኃላፊ ጋር ይወያያል፣ እና

   ሐ. አግባብ ያላቸውን ህጎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና የአሰራር ልምዶች በማገናዘብ የቀረበለትን ቅሬታ ያጣራል፤

መ. ኮሚቴው የምርመራውን ውጤትና የውሳኔ ማመልከቻውን ከቀረበለት ቀን ጀምሮ እጅግ ቢዘገይ አምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው ለርዕሰ መምህሩ ያቀርባል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 46. የማስረጃ ወጭ

1. የማስረጃዎች አቀራረብ የገንዘብ ወጭ የሚያስከትል ከሆነ ማስረጃው እንዲቀርብለት የሚፈልገው ወገን ለሚያቀርበው ማስረጃ የሚያስፈልገው ወጭ ራሱ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ተከሳሹ ማስረጃ ይሆኑኛል ያላቸው በትምህርት ቤት ይዞታ ስር ከሆነና በዲሲፒሊን ኮሚቴ እንዲቀርብ ከታዘዘ የሚያስከትለውን ወጪ እንዲሸፍን አይጠየቅም፡፡

### 47. ተከሳሽ የሚከራከርለት ሰው ለመወከል ስለመቻሉ

ተከሳሽ በዲሲፒሊን ወይም በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ላይ በሚከራከርበት ጊዜ የመረጠውን ሰው ይዞ ለመቅረብ፣ ለመወከል ወይም እንዲከራከርለት ለማድረግ መብት አለው፤ ይህንንም ተከሳሽ ለኮሚቴው በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

### 48. ተፈጻሚነት ስለማይኖረውሕግ

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ቢሮው ያወጣው መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈነ ጉዳይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 49.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው ድረ-ገፅ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ 2016 ዓ.ም**

**ዘላለም ሙላቱ /ዶ/ር/**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**ትምህርት ቢሮ ኃላፊ**